የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፬
አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.64
ADDIS ABABA 14th July, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፬/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ለበረሀ አንበጣ መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፉ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ………………………ገጽ ፲፪ሺ፮፻፸፱

## Content

Proclamation No.1214/2020

International Development Association Loan Agreement for financing Desert Locust Response Project Ratification Proclamation............Page 12,679

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፬/፪ሺ፲፪**

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለበረሀ አንበጣ መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ሃያ ሶስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር. (፳፫ ሚሊዮን ፩፻ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለምዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባው ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**PROCLAMATION NO. 1214/2020**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

WHEREAS, the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to Twenty Three Million One Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 23,100,000.00) for financing Desert Locust Response Project, was signed in Addis Ababa on 22nd day of May, 2020;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on 25th day of June, 2020;

NOW, THERFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለበረሀ አንበጣ መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለምዐቀፉ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፬/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለምዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 6651 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ሃያ ሶስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር. (፳፫ ሚሊዮን ፩፻ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for financing Desert Locust Response Project Ratification Proclamation No. 1214/2020".

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement Number 6651 signed in Addis Ababa on 22nd day of May, 2020 between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to Twenty Three Million One Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 23,100,000.00) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the *Federal Negarit Gazettee.*

**Done at Addis Ababa, on this 14th day of July, 2020**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**